# የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር
# Gambella People's United Democratic Front

ግንቦት 22 ቀን 99 ዓ/ም
May 30, 2007

## ከጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር የተሰጠ መግለጫ

## የወያኔ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር የሚኒሶታ፥ አሜሪካ ጉብኝት በታኅሣስ 3 ቀን 1996 ዓ/ም በጋምቤላ ሕዝብ ላይ የተፈጸመውን የጅምላ ጭፍጨፋ ቁስል እንዲያመረቅዝ የሚያደርግ ተግባር በመሆኑ እናወግዘዋለን።

አገራችን ኢትዮጵያ በሃያ-አንደኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ከገጠሚት ከባድ ፈተናዎች መካከል ከሦስት ዓመታት በፊት በወያኔ የበላይ ሹማምንት ታቅዶ፥ በዶ/ር ገበረሀብ በርነባስ አስፈጻሚነት የተተገበረው የታኅሣስ 3 ቀን 1996 ዓ/ም በጋምቤላ ክልል በአኙዋክ ምሁራን ላይ የደረሰው የጅምላ ጭፍጨፋና ምርጫ 97ን ተከትሎ በተለይ ወያኔን በግልጽና እሱም ሊሸፍነው ባልቻለ መልኩ በተፋው የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረው አሳዛኝ እልቂት ምን ጊዜም የማይረሳ፥ አበክረን የምንቃወመውና የምናወግዘው አረመኔአዊ ድርጊት ነው።

የአገዛዙ ባለሥልጣኖች ታኅሣስ 3 ቀን 1996 ዓም በጋምቤላ ሕዝብ ላይ ለፈጸሙት የጅምላ ጭፍጨፋና በምርጫ 97 ድምጹን በነፈጋቸውና መብቱ እንዲከበር በጠየቀው ሰላማዊ ወገናችን ላይ ላደረሱት አረመኔአዊ ግድያ፥ እንግልትና ወከባ ምንም ዓይነት ሃላፊነት ሳይሰማቸውና በንጹሃን ዜጎች ላይ ለደረሰው ግፍ ተጠያቂነት ሳይኖር፥ በሕዝብና ከሕዝብ ለሚነሱ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ሰላማዊ መፍትኄ በመሻት ፋንታ በማንአለብኝትና በትእቢት በተወጠረ መንፈስ የሽብር አገዛዝ ሥርዓቱን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በማስፈን የናጠጠ የሰብአዊ መብት ረገጣ ላይ ተሰማርተዋል። የአገዛዙ ቁንጮዎች በሕዝብ ላይ ያደረሱትንና እያደረሱ ያሉትን ሁለንተናዊ ግፍ ለማደባበስ የኢትዮጵያን ሕዝብና ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡን ለመደለል በተለያዩ ጊዜዎች የተለያዩ የማዘናጊያና አቅጣጫ የማሳሳቻ እርምጃዎችን ከመውሰድ አልበዘኑም። ይህንኑ የማወናበጃ ዘመቻም ከሚወዳት አገሩ ተሰዶ በውጭው ዓለም በሚኖረው ኢትዮጵያዊ ላይ ተያይዘውት ይገኛሉ። ይህ ኢትዮጵያውያንን በብሔር/ብሔረሰብ፥ በአካባቢ፥ ወዘተ... ባተኮረ መልኩ ለመለያየትና ለመከፋፈል ያነጣጠረ ዘመቻ ተግባራዊ መሆን የወያኔ ካድሬዎችና ተለጣፊ ሹማምንት ተሰማርተዋል።

ቀደም ሲል አዲሱ ለገሰን፥ አባዱላ ገመዳን፥ ዓባይ ፀሐየን፥ ወዘተ... እንዳሰማራ ሁሉ አሁን ደግሞ አዳዲሶቹ ተሰልፈዋል። በዋናነት ለመጥቀስ ያህል ዶ/ር ገበረሀብ ባርነባስን ከዓለም-አቅፍ ማኅበረሰብ እይታ  እንዲሰወር ወደ ቤተሰማያት መቀሌ ትግራይ ክልል ሲላክ ምትኩ የሆነውን አዲሱ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር የጋምቤላ ማኅበረሰብ አባላትን “ለማነጋገር” ሚኒሶታ አሜሪካ ገብተዋል። ከጉብኝቱ በኋላ ከፍተኛ አመኔታና ሃላፊነት የሚጠብቀው የሜራ ተዋናይ በአኙዋኮች ላይ የተፈጸመውን የጅምላ ጭፍጨፋ አጣጥሎ፥ የ97ቱ ምርጫ ድምዳሜ በወያኔ የበላይነት መረጋገጡን ሁሉ በውሸት ዴሞክራሲ ውዳሴ ከንቱውን በአየር ላይ እንደሚያስተጋባ አንጠራጠርም።

ከልምድ እንዳየነው በቅርቡ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የኦሮሞ፣ የአማራና የትግሬ ተወላጆች ለተባሉት ተመሳሳይ የቧልት አወናባጅ ዘመቻ እንደተሰበከላቸው ሁሉ፣ አገዛዙ ስለ ኢንቬስትመንት ፖሊሲ በጋምቤላ ስለሚሠመርበት ሁኔታ፣ ስለ ኢትዮጵያ ሚሌኒየም በዓል አከባበር፣ ስለ ወያኔ የግንቦት ሃያ 16ኛው ዓመት በዓል አከባበር፣ የኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች በዓል መከበርን፣ ስለ ኢትዮጵያ 3 ዙር የሕዝብና የቤቶች ቆጠራና ጠቃሚነት በሚያመለክቱ አንኳር አንኳር ቀልብ ይስባሉ የተባሉት ጉዳዮች ላይ ግንባር ለግንባር ቀርቦ ለመስበክ መምጣቱን ድፍረት ብቻም ሳይሆን ለመውደቅ የተቃረበው አገዛዝ ብርታት የሚሰጡት እየመሰላቸው በትርምስ ላይ ይገኛሉ። በሰለጠነው ዓለም የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ዓላማ ለዕድገት አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች የሚሰባሰቡበት ሲሆን አገዛዙ ግን የሽብር ሥርዓቱን በቀጣይ አሥር ዓመታት ውስጥ በማስፋት በጅምላ ጭፍጨፋና በኢሰብዓዊ መብት ረገጣ እየማቀቀ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በብሔር/ብሔረሰብ ለያይቶ የሚያጫርስበትን የውድመት 3ኛ ዙር የቤቶችና የሕዝብ ቆጠራ በሚተገበርበት ወቅት የሚደረግ በ"ጉብኝት" ስም የሚደረግ ሕዝብ ከፋፋይ ዘመቻ ስለሆነ አጥብቀን እናወግዘዋለን።

የጋምቤላ ሕዝብ ጥያቄ ሚኒሶታ ድረስ የሚያስመጣ ከፋፋይ ጉብኝት ሳይሆን ከታኅሣስ 3 ቀን 1996 ዓ/ም የግፍ ጭፍጨፋ ጀምሮ ከዚያም ወዲህ በክልሉ ስልከፈጸመው የ1200 ዜጎች እልቂት፣ ስለወደሙት ቤቶች፣ ንብረትና ማሳዎች፣ በየጎረቤት አገሮች ተሰድዶ የሚገኘው 15,000 አኙዋኮች፣ ከጅምላ ጭፍጨፋ ማግስት የክልሉ እራስን በራስ የማስተዳደር መብት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስለመጠለፉና ስለክልሉ አጠቃላይ ሰላምና መረጋጋት ስለሚመጣበት ሁኔታ ሰላማዊ የፖለቲካ መፍትኄ እንዲፈለግ በሦስተኛ አካል አደራዳሪነት የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር ከወያኔ መንግሥት ወኪሎች ጋር ውይይት ስለሚደረግበት ሁኔታ ማሰቡ የተሻለ እንደሚሆን ሳንጠቁም አናልፍም። ይህ የሰላማዊ ውይይት ጥሪ ደግሞ ድርጅታችን መሥራችና አባል በሆነበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት አማካይነትም ቅድመ-ምርጫ ጀምረን የወተወትንበት ጉዳይ ነው።

ሰላማዊ የትግል ስልት መርጦ በሚንቀሳቀሰው የክልሉ መሪ ድርጅታችን (ጋሕአዴግ) በክልሉም ሆነ በአጠቃላይ በአገራችን በኢትዮጵያ ላሉ የፖለቲካ ችግሮች የፖለቲካ መፍትኄ መንገድ አስፈላጊ መሆኑን የምንጠቁመው የወያኔን ደንታ ቢስነት ባለማወቅ ሳይሆን፣ ከምርጫ 97 በኋላ ልቡ በእብሪት ያበጠበት ወያኔ የሰላማዊ መንገዶችን ሁሉ ዘግቶ አገራችን ኢትዮጵያ ወደማያባራ የጦርነት እሳት ውስጥ እንድትገባ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ያስገደደበት ሁኔታ መኖሩንም እንረዳለን። ነገር ግን በባርነት ኖሮ በስደት ላይ ያለው በተለይ የአኙዋክ ሴቶችና ልጃገረዶች ክብረ ንጽህናቸውን በውጭ ዜጎች በግድ በመደፈርና ለወሲባዊ ባርነት ተዳርገው የሚገኙ ወገኖቻችን ጭንቀትና ብሶት እንዲወገድ በማሰብ በአሰቃቂ ስደት ላይ ያለው ወደ አገሩ እንዲመለስና ሰላማዊ ኑሮ እንዲመሠርት ስንል በወያኔና በጋሕአዴግ መካከል ሰላማዊ ውይይት እንዲደረግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመናል።

በአሃዳዊ የመንግሥት አወቃቀር መሠረተ ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ የጋምቤላ ክልል አሁን በወያኔ እየተሠራበት ያለው ከማዕከሉ የፌዴራል አካል ወደታች ብቻ በሚፈስ የግንኙነት ትስስር እንዲቆምና የሥልጣን ምንጭ ሕዝብ መሆኑን በተግባር በሚገልጽ ትርጉም ያለውና ከሥር ወደላይ በሚኖር ትክክለኛ ፌዴራላዊ አሠራር እንዲኖርና ሥልጣን ከማእከል ወደ ሕዝቡ ማለትም ወደ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ እንዲወርድ እንዲደረግ ድርጅታችን የሚጠይቀው፣ የሚያምንበትና የሚታገልለት ጉዳይ ነው።

የጋምቤላ ክልል የአገራችን የኢትዮጵያ አንድ አሥረኛ አካል ብቻ ሳይሆን ነባር አፍሪቃዊ መሬትም ነውና ሕዝባችን በጭቆና፣ በችግር፣ በፍርሃትና በመሸማቀቅ እንዳይኖርና በወያኔ የአፈናና የግፍ አገዛዝ ምክንያት የሌሎች አፍሪቃ አገሮች ዜግነት

በግዴታ እንዳይመርጥ በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለው የመከፋፈልና ያላባራ ጥቃት በአስቸኳይ እንዲቆም እንጠይቃለን። ይህ ሳይሆን ቀርቶ የዴሞክራሲ ሥርዓት የጠማው ሕዝባችን የራሱን ዕድል በራሱ ወስኖ እራሱንም አገሩንም እንዲጠቅም ዕድሉን ከተነፈገ በክልሉ ለሚከሰተው ቀውስ ተጠያቂ ወያኔ ብቻ መሆኑን እናስጠነቅቃለን።

ጠቅለል ባለ መልኩ የአፍሪቃ ኅብረት ለአፍሪቃ መንግሥታትና ሕዝቦች አንድነት መፍትሔ በሚሻበት በአሁኑ ወቅት፥ የወያኔ የከፋፍለህ ግዛ ተልእኮን ያነገበ የሚኒሶታ፥ አሜሪካ “የልማትና የኢንቬስትሜንት ጉብኝት” የከተማ አዳራሽ ስብሰባ ከፖለቲካ መፍትሔ በፊት ሊታሰብ የማይገባ ልዩነትን የሚያሰፋ መሰሪያዊ ነውረኛ ዘመቻ መሆኑን ስለምናምን እናወግዘዋለን።

በጋምቤላ ክልል የተከሰተው ፖለቲካዊም ሆነ ኤኮኖሚያዊ ችግሮች በቀረው የአገሪቱ ክፍሎች እንዳሉት ችግሮች ሁሉ አገር-አቀፍ በሆነ ደረጃ የጋራ መፍትሔ ሊፈለግላቸው እንደሚገባ እምነታችን ነው። የጋምቤላ ሕዝብ ላይ ደግሞ የተነጣጠረበት ዘመቻ የመኖርና የኅልውና ዋስትናው ይበልጥ አደጋ ላይ ስለወደቀ የትኩረት አቅጣጫችን በመሆኑ ድርጅታችን በሕዝባችን ላይ ያለውን ተጨባጭ ፈተና ሁሉም እንዲረዳልንና ድምፁን ከኛው ጋር እንዲያሰማ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን። በአገራችን ውስጥ ያሉ ችግሮቻችንን ለመፍታት አገዛዙ በልማትና በኢንቬስትመንት ስምም ይሁን በሌላ ሰበብ በመካከላችን ልዩነትን ለመፍጠር ለሚያደርገው የተንኮል ዘመቻ ሰለባ ሳንሆን፥ አንድነታችንን ጠብቀንና ልዩነቶቻችንን ወደጎን በማስቀመጥ ለሕዝብና ለአገር ስንል በውይይትና ትርጉም ባለው ድርድር የጋራ ሰላማዊና ፖለቲካዊ መፍትሔ እንዲፈለግ ጥሪያችንን ለሚመለከተው ሁሉ እናቀርባለን።

በጋምቤላ ሕዝብ ላይ የሚደረገው ጭቆናና ጭፍጨፋ ይቁም!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

የጋምቤላ ሕዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ግንባር